የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

የክርስትና ህይወት መርሆዎች
የጥናት መመርያ

# የወንጌል ስርጭት መንደርደርያ

## ትምህርት ፰፡ የወንጌል እዉንት ምንድን ነዉ - የሃጥያት ችግሩ

## መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀመዝሙርነት መርሖዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም “የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ” የሚል ነዉ። የዚህ ተከታታይ ትምሕርቶችን ያቀፈው ክፍል ዓላማ፣ ተሳታፊዎች ወንጌልን በብቃት ለሌሎች በማካፈል (በማሠራጨት) ዉጤታማ እንዲሆኑ፣ ማስታጠቅና ማዘጋጀት ነዉ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት (ለሚኒስትሪ) እንዴት እንደሚያስታጥቀን መረዳት፤ የወንጌል መልእክታችንን፥ ለተለያዩ የዓለም እይታ ወይም አመለካከቶች እንዴት እንደምናዘጋጅ እናስተዉላለን። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ዉስጥ የተገኘዉንና፤ የማይለወጠዉን የተስፋ መልእክት፥ ወይም የምሥራች ቃል፤አሁንም ገና ክርስቶስን ወደ አላወቀዉ ዓለም እንድናመጣ ይረዳናል።

ይህ የትምህርት መመርያ የተወሰን የትምህርት ክፍልን ብግላቸዉ በጥልቀት ለመመልከት የሚጥሩ ሰዎችን ለመድረስ ነዉ። ይህ ትምህርት www.DEamharic.org ላይ ከሚገኙት የደቀመዘሙራን መሰረታዊ ግባቶች ከሆኑት የምስል እና የ ድምጽ ስራዎች ጋር በቅንጅት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

---

በተለይ ካልተገለጸ በቀር፥ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓምከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድ ቶ የታተመ ነዉ።

**ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ** www.discipleshipessentials.org/ licensing **ይመልከቱ.**

# የወንጌል ስርጭት መንደርደርያ

## ትምህርት 8፡ የወንጌል እዉነት ምንድን ነዉ – የሃጥያት ችግሩ

### ስለምንድን ነዉ?

ወንጌልን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማድረስ ልንረዳዉ እና ስለምን እንደሆነ መረዳት የግድ ያስፈልገናል። ወንጌል በአለም ላይ ላለዉ የሃጥያት መፍትሄ ነዉ።.

### ታዉቀዉ ዘንድ ...

ሃጥያት ከተጀመረ ግዜ ጀምሮ  እግዚአብሄር ሃጥያትን የሚያሸንፍበት እና ወሎ አድሮም ሞትን ድል የሚነሳበት መንገድ አለዉ። ይህ ትምህርት ችግር ስለሆነዉ ሃጥያት እና መፍትሄ ስለሆነዉ ወንጌል ነዉ ዳሰሳ የሚያደርገዉ።  የምናቀርበዉ እዉነታ አንገብጋቢነት በጊዜ ሂደት እየተረዳን እያለ በተስፋ እና በጽናት መቆም ግን አስፈላጊ ነዉ። እግዚአብሄር በህይወት ቃላት እና በይቅርታ ሞልቶናል፡ እነኝህን ቃላተ እስከአሁን ድረስ ላላመኑት ልናደርስላቸዉ ይገባል። መጽሃፍ ቅዱስ የሰይጣንን የጥፋት እና የሞት እቅድን በምን መልኩ ልናልፈዉ እንደምንችል ይገልጽልናል። ምንም እንኳዋን ማመን ቢሳናቸዉም ሰዎች ሃጥያተኞች ናቸዉ:: የሃጥያት ዉጤት የሆኑትን እንደ ሞት፣ ስቃይ፣ ብቸኝነት እና ፍርሃትን በአካባቢያቸዉ ሊመለከቱ ይችላሉ። ከዚህ ሁሉ ከፉ ማምለጥ የማይ ማን አለ? ይህንን ትምህርት በምታጠና ግዜ እግዚአብሄር ስለወንጌሉ አዲስ መጓጓት እና ስሜት ይሰጥሕ ዘንድ ጸሎት አድርግ።

# ጀምር

**1.** በቅርቡ የተቀበልከዉ መልካም ዜና ምንድን ነዉ? ያንን ዜና ማን ነበር ያካፈለህ? የአንተስ ምላሽ እንዴት ያለ ነበር? ዜናዉን ምንድን ነበር መልካም ያደረገዉ ?

**2.** በራዲዮ ወይ በተለቪዢን የሚነበቡ ዜናዎችን አድምጠህ ታዉቃለህ? ወይንም ጋዜጣ አንብበህ ታዉቃለህ ?  በአለማችን ላይ መልካም ዜና ነዉ መጥፎ ዜና የሚበዛዉ ?  ለምንደን ነዉ መጥፎ ዜናዉ ከጥርፉ ዜናዉ በላይ ጎልቶ የሚታየዉ ?

# ጥናት

❖ **ወንጌል የሚለዉ ቃል ምን ማለት ነዉ ?** ወንጌል የሚለዉ ቃል “መልካም ዜና” ማለት ነዉ። ይህ ዜና ለእያንዳንዳችን መልካም ዜና ነዉ። እያንዳንዳችን ተመሳሳይ ችግር ነዉ ያለበን። ወንጌል ደግሞ መፍትሄዉ ነዉ።

➢ ወንጌል በእግዚአብሄር የተሰጠ እንጂ በሰዉ የተፈለሰፈ አይደለም። በመለከታዊ ሃይል የተቀኘ ወይንም የእግዚአብሄር ትንፋሽ ነዉ።(2ኛ ጢሞቲዎስ 3:16)  አስፍተዉ ሲመለከቱት ወንጌል ማለት መጽሃፍ ቅዱስ በሙሉ ማለት ነዉ ₉ሁሉም ቅዱሳን መጽሃፍት)።

➢ የእግዚአብሄርን የመዳን እቅድ እናምን ዘንድ መጸሃፍ ቅዱስ በእግዚአብሄር ቃል የተቀኘ መሆኑን ማመን ገደ ይላል። ከእዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥቅሶች በመጀመርያ ደረጃ ወንጌልን እንዴት እንደተቀበልን የሚለዉ ምን አለ? እኒህ ጥቅሶች ታማኝ የሆኑት ለምንድን ነዉ ?

| | |
|---|---|
| ወደ ገላትያ ሰዎች 1:11-12 | |
| 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:13 | |
| 1ኛ ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች 2:7-10 | |

❖ **ወንጌል ለምን ነበር የተሰጠዉ?** ወምጌል የተጻፈበት አላማ እኛን ወደ እግዚአብሄር የምንመለስበትን መንገድ ለማሳየት ነዉ። እኛ የተፈጠርነዉ ድልን ለእግዚአብሄር ለመስጠት ነዉ። እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ምመወዳጀትን ሁሌም የሚሻዉ ነዉ። ብሎም በእኛ ህይወት ዉስጥ መወደስን እና መሞገስን ይወዳል። እኛ እንደ አንድ የቤተሰቡ አባል እና በአምሳሉ የተፈጠርን ነን። እኛ የተፈየርንለት አላማ ይህ ነዉ።

➢ ለተፈጠርንለት አላማ ከኖርን ማለተም ከታዘዝን እና ከፍ ከፍ ካደረግነዉ እግዚአብሄር የገባልን ቃል መንድን ነዉ፧

| | |
|---|---|
| የማቴዎስ ወንጌል 11:28-29 | |
| ትንቢተ ኤርሚያስ 29:11 | |
| የዮሃንስ ወንጌል 14:27 | |

❖ **ችግሩ ምንድን ነዉ ?** የኛ ከእግዚአብሄር ጋር የነበረን ወዳጅነት የደፈረሰዉ ሃጥያት ወደ ምድር የገባ ገዜ ነዉ። ሃጥያት እኛን ከእግዚአብሄር ከመለያየቱም በላይ ከእርሱ ጋር የነበረንን ወዳጅነትን ንዶታል። እያንዳንዱ የሰዉ ዘረ የሚጋራዉ ችግር ይህ ነዉ;፡

- መጽሃፈ መክብብ 7:20 እና ወደ ሮሜ ሰዎች 3:10 አንብብ።:ከእነኝህ ጥቅሶች በመነሳት ማን ነዉ ሃጥያተኛዉ?

- ይህ ሃጥያት እኛን ከእግዚአብሄር ለያየን። ይህ ሃጥያት እኛን ከእግዚአብሄር ለያየን ብሎም እሱ ለእኛ የነበረዉን እቅድ አፋለሰዉ። እኛ እራሳችንን ከእግዚአብሄር የምናስቀድም ከሆነ እንደእግዚአብሄረቅድ መኖር ፍጹም አይቻለንም።

❖ **ሃጥያት ወደ ምድር እንዴት እንደገባ:** ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል ባሰብክ ግዜ ልትረሳዉ የማይገባህ ሌላዉ ቁልፈ ሃሳብ በመጀምረያ እንዲህ ያለ ምስቅልቅል ዉስጥ እንዴት እንደገባን ነዉ።ስለተወሳሰበዉ የመዳን ህሳቤ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖር ሃጥያት ወደእዚህ አለም እንዴት እንደገባ ጥንቃቄ በተሞላዉ መንገድ ማብራራቱ ጠቃሚ ነዉ። ከዛም በላይ የተለየ አለማዊ እይታ ያላቸዉ ሰዎች የተሳሳተ ህሳቢያቸዉን ገልጦ የማሳየቱ ስራ መንደርደርያ ሊሆን ይችላል።

- ስለሚከተሉት ነጥቦች እርግጠኛ ልንሆን ይገባል:

| | |
|---|---|
| *የአዳም ሃጥያት በያንዳንዱ የእርሱ ዝርያ ላይ ለተከተለዉ አካላዊ እና መንፈሳዊ ሞት ምክንያት ነዉ።* | ኦሪት ዝፍጥረት 3:1-7; ኦሪት ዝፍጥረት 3:19 |
| *በአዳም አማካኝነት ሃጥያት ወደ ሰዉ ዘር ገባ* | ወደ ሮሜ ሰዎች 5:12 |
| *የሰዉ ልጅ በተፈጥሮው ሃጥያተኛ ነዉ.* | ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:3 |
| *የሰዉ ልጆች በሙሉ ሃጥያት መስራታቸዉን ይቀጥላሉ* | ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23; መዝሙረ ዳዊት 14:3 |
| *ከሃጥያታችን የተነሳ በመንፈስ ሙዉት ከመሆናችንም በላይ በእግዚአብሄር ፊት መኖር አይቻለንም* | ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-5 |
| *እግዚአብሄር ፍጹም እና ቅዱስ ስለሆነ የትኛዉም ሃጥያት ቅጣቱን ሳያገኝ አያልፍም።* | ኦሪት ዝዳግም 32:4; ወደ ሮሜ ሰዎች 1:18 |
| *የሃጥያት ዋጋዉ ሞት ነዉ።.* | ወደ ሮሜ ሰዎች 6:23 |

- የእግዚአብሄርን ይቅርታ ካላገኘን በስተቀር የሃጥያትን ውንጀላ ልናመልጥ አይቻለንም ። ሰይጣን ሁልገዜም እኛን ለማሳት እና የእግዚአብሄርን ፍቃድ እንዳንሞላ ለማድረግ መሞከሩን አይተዉም። ለሆነ ሰዉ ወንጌልን እያካፈልክ ከሆነ እና ያ ሰዉ ሰይጣን ለህይወቱ ካዘጋጀለት እቅድ ማምለጥ የሚሻ ከሆነ ይህ ሰዉ በእርግጠኛነት የእግዚአብሄርን እቅድ ለመስማት በጣም ጉጉ ነዉ የሚሆነዉ። እግዚአብሄር ሃጥያትን እና ሞትን ለአንዴ እና ለመጨረሻ የሚያሸንፍበት እቅድ አለዉ።

| ሰይጣን ለእኛ ያለዉ እቅድ | እግዚአብሄር ለእኛ ያለዉ እቅድ |
|---|---|
| • ጸጸት<br>• ሃሳብ<br>• ሃጥያት<br>• ሞት<br>• ስቃይ<br>• የሃጥያት ባርያ መሆን<br>• ከእግዚአብሄር እስከዘላለሙ መለያየት | • ሰላም እና ደስታ<br>• በፈተን ግዜ እርዳታ<br>• ቅዱስ ህይወት<br>• የተትረፈረፈ ህይወት<br>• ለሃጥያት ይቅርታ<br>• በእየሱስ ነጻነት<br>• የዘላለም ህይወት ከእየሱስ ጋር |

➢ ሃጥያት በአለማችን ለምን ችግር እንደሆነ አብራራ?

➢ እኛ በሃጥያት ዉስጥ ተዘፍቀን እንድንኖር የሰይጣን እቅድ መሆኑ ለምን ነዉ ?

እግዚአብሄር ከ እርሱ ጋር ከእኛ ጋር ወዳጅነት ይኖረዉ ዘንድ እና እናም በርሱ የተትረፍርፍ ህይወትን እናጣጥም ዘንደ ፍላጎቱ ነዉ። ነገር ግን ሃጥያታችን ከእርሱ የለያየን ሲሆን ይቅርታዉ ያስፈልገናል። እግዚአብሄር የወደደዉን ህይወት እንዳንኖር ሰይጣን የተቻለዉን ሁሉ ያደርጋል። ለሃጥያታችን የምንከፍለዉ ዋጋ ለዘለአለም ከእግዚአብሄር መለየትን ነዉ። ነገር ግን እየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፋንታ በመሞት ስለእኛ እርሱ ዋጋን ከፍሏል። ይህ የወንጌሉ መልእክት የመጀመርያዉ ክፍል ነዉ።

### ክለሳ

- ‘ወንጌል’ የሚለዉ ቃል ‘መልካም ዜና’ ማለት ነዉ። ይህ መልካም ዜና ደግሞ ለሁላችን ነዉ። ምክንያቱም ሁላችንም አንደአይነት ችግር ስላለብን።
- ችግሩ ሃጥያት ሲሆን መፍትሄዉ ደግሞ እየሱስ ነዉ።
- እግዚአብሄር ለእኛ አስደናቂ እቅድ አለዉ። ነገር ግን ሃጥያት መስራታችንን የምንቀጥል ከሆነ ከእርሱ ጋር የሚኖረን ወዳጅነት የተሰበረ ይሆናል።
- ሃጥያት ወደ ምድር በአዳም በኩል ገባ። ከዛን ግዜ ጀምሮ ከሃጥያት ጋር ነዉ የምንወለደዉ።

የሃጥያት ዋጋዉ ሞት ነዉ። እንደሰራነዉ ሃጥያት ከሆነ ሁላችንም ከእግዚአብሄር መነጠል ይገባናል።፡ነገር ግን እግዚአብሄር በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቸኛዉን መፍትሄ ሰጥቶናል።

# የማመሳከሪያ ጥያቄዎች

1. መልካም ዜናን ከምትሰብከበት መንገዶች ጥቂቶቹ እንዴት ያሉ ናቸዉ?

2. አማኝ ያልሆኑ ጓደኞችህ ስለሃጥያታቸዉ ውንጀላን ባልተቀኘ መልኩ እንዴት አድርገህ እንዲያውቁ ማድረግ ትችላለህ? እንዴት ያሉ ጥያቄዎችን ልትጠይቃቸዉ ትችላለህ? ስለራስህ ህይወት ምን ልትነግራቸዉ ትችላለህ?